Alexandria ከተማ፣ Virginia

# በአሌክሳንድሪያ የፖሊስ አገልግሎት ላይ የሚደረግ የማህበረሰብ ክትትል

የህብረተሰባዊ ተሳትፎ ስብሰባዎች

የካቲት 27 እና መጋቢት 3/2021

# በሰኔ 9/2020 ውሳኔ ቁጥር 2950 በተሰጠ የምክር ቤቱ መመሪያ

- በአሌክሳንድሪያ የማህበረሰብ ፖሊስ ክለሳ ቦርድ ተቋቋመ

- የከተማ ሥራ አስኪያጅ የሆኑትን እና የከተማውን ዐቃቤ ሕግ ወደምክር ቤቱ በመጀመሪያው የሕግ ረቂቅ ስብሰባ መስከረም ወር ላይ በመቅረብ በአሌክሳንድሪያ ውስጥ በማህበረሰቡ የሚደረግ የፖሊስ አገልግሎት ክትትልን ለማስጀመር የሚሆኑ ህገደንቦችን ምክረአሳብ እንዲያቀርቡ መመሪያ ተሰጠ

# ከጠቅላላ ጉባዔው የተውጣጣ የህግ አርቃቂ ባለስልጣን

- በሴኔት ቢል 5035 (ሃሽሚ)፣ የምክር ቤት ቢል 5055 (ኼሪንግ) ለአከባቢዎቹ ማህበረሰቡ የሚከታተሉ አካላትን እንዲያዋቅር ስልጣን ሰጥቷል
- የእነዚህ አካላት ስልጣናት፣ በማህበረሰባቸው ውስጥ ስላለው የሕግ ማስከበር ተግባር ያላቸውን ግኝት መቀበል፣ መመርመር እና መስጠት ሆኖ
- የሕግ ማስፈጸም ፖሊሲዎችን፣ ትግበራዎችን እና ሥነሥርዓቶችን በመመርመር ምክሮችን ይሰጣል
- በሐምሌ 1/2021 ስራ ይጀምራል

# በፖሊስ አገልግሎት ላይ
# የማህበረሰብ/ሲቪል ክትትል የሚባለው ምንድነው?

- ከሲቪል የማህበረሰቡ አካላት የተውጣጡ አካላትን ሆኖ ተግባራቸው በዚያ ማህበረሰብ ውስጥ በክትትል፣ በቁጥጥር እና/ወይም በምርመራ የሚከተሉትን የሚቆጣጠሩ ናቸው

- በበላይነት መምራት
- ተጠያቂነት
- ግልጽነት

# በፖሊስ አገልግሎት ላይ የማህበረሰብ/ሲቪል ክትትል ለምን አስፈለገ?

- ስለፖሊስ አገልግሎት ህዝቡ ያለውን አመኔታ ለማጎልበት
- በፖሊስ ምርመራዎች ወቅት ግልጽነት እና ቅንነት መኖሩን ለማረጋገጥ
- እልባት የሚያስፈልጋቸው ስልታዊ የሆኑ ነገሮች ስለመኖራቸው ማረጋገጥ
- እጅግ ሙያዊ የሆነ፣ ትክክለኛ እና ቀልጣፋ የፖሊስ አገልግሎት በተቻለ መጠን ለማህበረሰባችን የሚያቀርብ ስርዓት በመፍጠር ድጋፍ ለማድረግ

# በፖሊስ አገልግሎት ላይ የማህበረሰብ/ሲቪል ክትትል ሞዴሎች

- ምርምር
- ግምገማ
- ኦዲት
- ቅይጥ

# ግምገማ ተኮር
# የፖሊስ አገልግሎት ክትትል

- በጣም መሠረታዊ የሚባለው የፖሊስ አገልግሎት ማህበረሰባዊ ክትትል
- የተጠናቀቁ ምርመራዎችን በመገምገም፣ ስለግኝቶቹ ምክርን ይሰጣል
- ከማህበረሰቡ የተውጣጣ ቦርድ፣ ከበጎ ፍቃደኛ ዜጎችን ተዋቅሮ፣ የተጠናቀቁ የውስጥ ጉዳይ ምርመራ ቅሬታዎችን ይገመግማል
- ቦርዱ በደምሳሳው የምርመራዎችን ትክክለኛነት፣ ሙሉዕነት፣ ገለልተኛነት በሚመለከት አስገዳጅ ባይሆንም ምክር ይሰጣል
- ከምርመራዎቹ በመነሳት ስለተወሰዱት የስነምግባር እርምት እርምጃዎች በቂነት ምክሮችን ይሰጣል

# ምርመራ ተኮር
# የፖሊስ አገልግሎት ክትትል

- ቅሬታዎችን ይቀበላል፣ ምርመራ ያደርጋል እንዲሁም ድምዳሜዎችን ያወጣል
- ከህግ አስፈጻሚው ወኪል ተገልሎ ስራውን ያከናውናል
- በተለምዶ ገለልተኛ የሆነ የከተማው ኤጀንሲ ነው
- በህግ አስፈጻሚ መኮንኖች ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን በተመለከተ በሕጉ መሠረት በገለልተኝነት ምርመራዎችን በማድረግ፣ ከማህበረሰብ ሠራተኞች ተውጣጥተው
- ለአጠቃላይ የሕግ ማስፈጸም ተግባሩ ክንውን የሚደረጉ ምርመራዎችን በሙሉ ከፖሊስ የውስጥ ጉዳይ ተተክተው ሊሰሩ ይችላሉ

# ኦዲት ተኮር
# የፖሊስ አገልግሎት ክትትል

- በስልታዊ ሁኔታ የፖሊስ አገልግሎቱን ተሃድሶ በመስራት ላይ ወደማተኮር ያዘነብላል
- ክስተቶችን አንድ በአንድ ሳይሆን የፖሊስ አገልግሎት ልማድ እና አተገባበሮች ላይ ያተኩራል
- የቅሬታ ምርመራዎችን ልማዶች ይመረምራል
- በምርመራዎች ጥራት፣ በግኝቶቻቸው እና በስነምግባር እርምት ውስጥ አግባብነት ያላቸውን ልማዶች ይፈልጋል
- ምክሮችን ይሰጣል
- እያንዳንዳቸውን አሳሳቢ ክስተቶች ወይም የቅሬታ ምርመራዎች ይከታተላል ወይም ይገመግማል

# ቅይጥ የፖሊስ አገልግሎት ክትትል

- ከምርመራ፣ ከግምገማ እና ከኦዲት ተኮር ሞዴሎች በከፊል ተጣምረው ይገኙበታል
- በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈለገውን እና የሚያስፈልገውን የክትትል ሚዛን ለማግኘት ሲባል ለአንድ ማህበረሰብ በተለየ ሁኔታ የተመረጠ ውህደት ይኖረዋል
- አንዳንድ ተመራማሪዎች ቅይጥ የሆነውን ሞዴል “ዓይነተኛ የፖሊስ ግምገማ ስርዓት” ብለው ይጠሩታል

# ውጤታማ የሆነ የፖሊስ አገልግሎት ክትትል ቁልፍ መገለጫዎች

- ገለልተኛነት
- በቂ የገንዘብ አቅም
- አሳሳቢ መረጃዎችን ማግኘት መቻል
- በቁልፍ ሹማምንት ዘንድ ዕውቅና መቸር
- አስተማማኝ ስልጣን መኖር
- ግልጽነት
- የማህበረሰብ/ባለድርሻዎች ድጋፍ እና ተደራሽነት
- ፖሊሲዎችን፣ ስልጠናዎችን እና ሌሎች ስልታዊ ጉዳዮችን መከለስ መቻል

# ቁልፍ ባህርያት

- “አንድን የማህበረሰብ ፖሊስ ግምገማ ቦርድ ለማየት ከበቃችሁ ያያችሁት አንድ የማህበረሰብ ፖሊስ ግምገማ ቦርድ ነው”

- አገልግሎት ሊያቀርብለት ለተመረጠለት ማህበረሰብ ልዩ መሆን አለበት
  - የዚያን ማህበረሰብ ፍላጎት፣ ጭንቀት፣ አመለካከት እና ችግሮች ለመፍታት አስፈላጊ የሆነ አድማስ እና ስልጣን ያለው መሆን አለበት
  - የአከባቢውን ባለድርሻዎች በማሳተፍ እና በጠንካራ የማህበረሰብ ግብዓት ላይ የተመረኮዘ መሆን አለበት

# የአሌክሳንድሪያ ማህበረሰባዊ የፖሊስ አገልግሎት ግምገማ ቦርድ፤ ዓላማው

- የአሌክሳንድሪያን የፖለስ አገልግሎት ሕጋዊነት ማጎልበት
- በፖሊስ መምሪያው፣ በከተማው ምክር ቤት፣ በከተማ ስራ አስኪያጅ እና በማህበረሰቡ መካከል እና ውስጥ ያለውን አመኔታ መጨመር እና ማጠናከር

# የአሌክሳንድሪያ ማህበረሰባዊ የፖሊስ አገልግሎት ግምገማ ቦርድ፤ ዓላማዎች

- ወቅቱን የጠበቀ፣ ፍትሐዊ እና ዓላማ ያለው የፖሊስ አገልግሎት ፖሊሲዎች፣ ልማዶች፣ ስነሥርዓቶች እና ውጤቶችን ግምገማ እና ምዘና በአሌክሳንድሪያ ውስጥ ማቅረብ
- ሊያገኟቸው የሚችሏቸውን አድሏዊ የሆኑ ልማዶችን፣ ማለትም ዘረኝነት እና ማህበራዊ የሆኑ ግድፈቶችን ለማረም የሚያስችሉ ትርጉም ያላቸውን መምልከታዎች እና የማስተካከያ ምክሮችን መስጠት
- በሚሰጡ የምክር ተግባራት እና ተሃድሶ አማካይነት ሁሉም የማህበረሰብ ክፍል፣ የወንጀል ፍትህ ሥርዓቱን ጨምሮ፣ መጠበቁን ማረጋገጥ
- እነዚህን ተሃድሶዎች በውጤታማ ሁኔታ ለመተገበር የሚሆኑ ስልቶችን መምከር

# የአሌክሳንድሪያ ማህበረሰባዊ የፖሊስ አገልግሎት ግምገማ ቦርድ፤ አድማስ እና ተግባራት

- ስለኃይል አጠቃቀም፣ ከህልፈተ ህይወት ጋር የሚገናኙ ክስተቶች እና ከባድ የስነምግባር ጥሰት ክስተቶችን የሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ አስተዳደራዊ ምርመራዎችን የማድረግ ስልጣን
  - ጠርቶ የማነጋገር ስልጣንን የሚጨምር የምርመራ ስልጣን
  - ቦርዱ የስነምግባር እርምት እርምጃ ሊመክር ይችላል
- በአሌክሳንድሪያ የፖሊስ መምሪያ (ኤ/ፒ/ዲ) በኩል የተከናወኑ ምረመራዎችን ሙሉዕነት በተመለከተ ሙሉ አስተዳደራዊ ምርመራ በማድረግ የመከለስ ስልጣን
- የፖሊስ አገልግሎት ልማዶች፣ ፖሊሲዎች፣ ሥነሥርዓቶች እና ውጤቶች ላይ በአሌክሳንድሪያ ውስጥ የመገምገም ስልጣን፤ ግኝቶችን የማሳወቅ፤ እንዲሁም ተፈጻሚ የሚደረጉ፣ ምክር የሚሆኑ አስተያየቶችን በአለክሳንደሪያ ስላሉ የፖሊስ አገልግሎት ልማዶች፣ ፖሊሲዎች እና ሥነሥርዓቶች መስጠት

# የአሌክሳንድሪያ ማህበረሰባዊ የፖሊስ አገልግሎት ግምገማ ቦርድ፤ የመግባቢያ ሰነድ

- ቦርዱ ከአሌክሳንድሪያ የፖሊስ መምሪያ ጋር የመግባቢያ ሰነድ የሚፈርም ይሆናል
- የግንኙነታቸውን እንዲሁም በቦርዱ እና በኤ/ፒ/ዲ መካከል ስለሚኖረው የጋራ ግዴታ ደንብ ይቀረጻል
- ቦርዱ ስራውን በገለልተኛነት መስራቱ የሚረጋገጥ ቢሆንም፣ ከሌሎች የከተማው አስፈላጊ ሥነሥርዓቶች ጋር ተቀናጅቶ - ለሁላችንም በአንድነት እንድንሰራ ድጋፍ የሚያደርግልን ይሆናል

# የአሌክሳንድሪያ ማህበረሰባዊ የፖሊስ አገልግሎት ግምገማ ቦርድ፤ አባልነት

- ሰባት የቦርድ አባላት በከተማው ምክር ቤት ይሾማሉ
- የከተማው ነዋሪ የሆኑ
- ፍትሐዊነት፣ ዓላማ መርነት፣ ቅንነት
- ከቦርዱ ተግባራት ጋር አግባብነት ያለው ልምድ
- ፍትሐዊ የሆነ፣ ዓላ መር፣ ገለልተኛ፣ የተሰባጠረ እና ወካይ የሆነ አካልን ይፈጥራሉ

# የአሌክሳንድሪያ ማህበረሰባዊ የፖሊስ አገልግሎት ግምገማ ቦርድ፤ አባልነት

- ቢያንስ ሦስት አባላት በአሌክሳንድሪያ ውስጥ የሚያስከፋ የፖሊስ አገልግሎት ካጋጠማቸው በታሪክ በዘር ወይም በህብረተሰብ ደረጃ ከተገለሉ ማህበረሰቦች መካከል የመጡ የሚደረግ ይሆናል
- ቢያንስ አንዳቸው ቢያንስ ሦስት አባላት በአሌክሳንድሪያ ውስጥ የሚያስከፋ የፖሊስ አገልግሎት ካጋጠማቸው በታሪክ በዘር ወይም በህብረተሰብ ደረጃ ከተገለሉ ማህበረሰቦች ጋር በተያያዘ የዘር ወይም ማህበራዊ ፍትህን ከሚሻ ወይም በሌላ ሁኔታ ከሚከራከርላቸው ድርጅት፣ መስሪያ ቤት ወይም ወኪል የመጣ አባል የሚደረግ ይሆናል
- ቢያንስ አንድ አባል በሕግ ማስከበር፣ በወንጀል ፍትህ ወይም በፖሊስ አገልግሎት ውስጥ ልምድ ያለው በሕጉ መሠረት የቦርዱ ድምጽ የማይሰጥ አባል የሚደረግ ይሆናል

# የአሌክሳንድሪያ ማህበረሰባዊ የፖሊስ አገልግሎት ግምገማ ቦርድ፤ ስታፍ አወቃቀር

- የፖሊስ አገልግሎት ኦዲተር
- መርማሪዎች
- ከከተማው የዐቃቤ ሕግ ጽህፈት ቤት የሕግ አገልግሎት ክፍል
- ከውጭ የህግ አማካሪዎች ድጋፍ የሚያደርግ

# የአሌክሳንድሪያ ማህበረሰባዊ የፖሊስ አገልግሎት ግምገማ ቦርድ፤ ቀጠያይነት ያላቸው ውይይቶች

- አጠቃላይ ረቂቅ የሥነሥርዓት ሂደቱ በመታየት ላይ ይገኛል
  - የቦርድ አባላት እና ሥነሥርዓቶች
  - የወንጀል ምርመራ በሚኖርበት ጊዜ ደግሞ የአስተዳደር ምርመራዎች ጊዜ
  - የምርመራ ቁሳቁሶች ምስጢር አያያዝ
- የምክር ቤት አባል ከሆኑት ሰይፈልዲን የተገኙ ነገሮች ዝርዝር የሆኑ ምክሮች፣ በድረገጽ ላይ የሚለጠፉ ለውጦች

# የማህበረሰቡ ግብዓት

- “አንድን የማህበረሰብ ፖሊስ ግምገማ ቦርድ ለማየት ከበቃችሁ ያያችሁት አንድ የማህበረሰብ ፖሊስ ግምገማ ቦርድ ነው”

- ለማህበረሰቡ የተለዩ መሆን አለባቸው
  - የዚያን ማህበረሰብ ፍላጎት፣ ጭንቀት፣ አመለካከት እና ችግሮች ለመፍታት አስፈላጊ የሆነ አድማስ እና ስልጣን ያለው መሆን አለበት
  - የአከባቢውን ባለድርሻዎች በማሳተፍ እና በጠንካራ የማህበረሰብ ግብዓት ላይ የተመረኮዘ መሆን አለበት

- በተለይ አሌክሳንድሪያን ፍላጎቶች፣ ጭንቀቶች፣ አመለካከቶች፣ ችግሮች እና ባህርያት የሚስማማ የሆነ የማህበረሰብ ፖሊስ አገልግሎ ግምገማ ቦርድ ለማዘጋጀት ዕድል ይፈጥራል

# ቀጣይ እርምጃዎች

- ምክር ቤቱን ለመምከር እና በምክር ቤቱ እሳቤ መሠረት ረቂቅ ህግጋት ለማስፈጸም ከማህበረሰቡ የተሰበሰቡ ግብዓቶችን መጠቀም
- ተሰብስበው ገቢ የተደረጉ የማህበረሰቡ ግብዓቶች በድርገጽ ላይ ይለጠፋሉ
- የማህበረሰቡን ግብዓት ለምክር ቤቱ እንዲታዩ፣ ከታሰቡት ህገደንቦች ጋር ህግጋት ጋር፣ መጋቢት 9 ቀን በከተማ ምክር ቤት የህግ ማርቀቂያ ስብሰባ ጊዜ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲነበቡ ማቅረብ
- ህግጋቱን በመጋቢት 13 የምክር ቤቱ ህዝባዊ መድረክ ላይ በማቅረብ በህዝባዊ መድክ እንዲጸድቁ ቀጠሮ መያዝ